# የቴዎድሮስ መታሰር እና "ኢትዮጵያዊነት"

(ዳዊት አበሩ)

በአገራችን በሥልጣን ላይ የተደላደለው  የእብሪተኞች ቡድን አምበል ከዕለት ወደ ዕለት ባህርዩ ጨርሶ የለየለት እብደት እየሆነ እንደመጣ ሁላችንም እያየን ነው። እንደ መለስ ዜናዊ ዓይነት የኢትዮጵያዊነትነትን ስብዕና ጨርሶ ሳይገድል ላያንቀላፋ ምሎ ለተገዘተ ደመኛ፣  የኢትዮጵያዊነት ምልክቶች ሁሉ የኀሊናው ቁስል፣ የገላው ህመም፣ የአዕምሮው ንውዘት እና አለመታደል ሆኖ ደሞ የቂም በቀሉ ሁሉ መወጫ ናቸው። የአንድነት ስሜት፣ ያብሮነት ተስፋ፣ የእርቅ ስነልቦና  እና የጋራ ብሔራዊነት አስተሳሰቦች፣ ምልክቶች፣ ተግባራትና ዕምነቶች ሁሉ ላለፉት 18 ዓመታት በቁጣውና በቂም በቀሉ በትሮች ያልርህራሄ ሲጨፈጨፉ እንደነበር ማንኛችንም አንስተውም። በዚህ ነፍሱን እንደ ክፉ ዛር በሚያንዘፈዝፋት የኢትዮጵያዊነት ስሜት ጥላቻ ከመጣበት መለስ በምድር ላይ ለማንም ምኅረት እንደሌለው ሁላችንም ዓይተናል። እንደ አሥራት ዓይነት ያገር መኩሪያ፣ እንደ ጺጋዬ ያለ ያገር ሃብት፣ እንደ ስዬ ያለ ያገር ጀግና፣ እንደ ገብሩ ያለ የሉዓላዊነት አርበኛ፣ እንደ ብርሃኑ ያለ ያገር ተስፋ፣ እና ሌሎችም ኀልቆ-መሣፍርት የሌላቸው ኢትዮጵያውያን ምን ያህል በዚህ መብረጃ የሌለው የመለስ ዜናዊ የቂም በቀል በትር የህይወት መስዋዕትነት እስከመክፈል ድረስ እንደተቀጠቀጡ ባይናችን ዓይተናል። በከፋ መልኩ ደሞ፣ ለበቀል ዱላው ሕጋዊ መልክ ለመስጠት ለያንዳንዳቸው በየጉዳያቸው እንዴት ዓይነት 'ልክ የተሰፋ' ልብስ እንደተዘጋጀላቸው የምንረሳው አይመስለኝም።

በዓለም ታሪክ ምናልባት ለመጀመሪያ ጊዜ ያገር መሪ ሆኖ ያንኑ የሚመራውን አገር የብሔራዊነት ምልክቶች ሁሉ አምርሮ በሚጠላ መሪ በቀል እንሰቃይ ዘንድ ለምን እንደተረገምን አላውቅም። መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያዊነት ስሜት ላይ ባለው ወደር የሌለው ጥላቻ ምክኒያት መሪ ከሆነበት ዕለት አንስቶ ያለማቋረጥና በሙሉ ሃይሉ ይሄንን አስተሳሰብ ለመግደል፣ አብሮ የመኖርንና የጋራ ብሔራዊነት ስሜትን ለማጥፋት ያላደረገውን ነገር መቁጠር የሚቀል ይመስለኛል። ለዚህ ፅሁፍ አስፈላጊ ቢሆንም እንኳን እጅግ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ስለተባለ "ባንዲራ ጨርቅ…" ፣ " የአክሱም ሃውልት ለወላይታው…" ወዘተ እያልኩ ላሰለቻችሁ አልፈልግም። ቁምነገሩ ሁላችንም እንዴት አድርጐ ያገራዊነት እሴቶቻችንን ሁሉ በረቀቀ መንገድ ከምድረ-ገፅ ለማጥፋት ሌት ተቀን እንደሚተጋ በየምክኒያቱ ለማየት መረገማችን ነው።

ድሮ ትምህርት ቤት የከበደ ሚካኤል መፅሐፍ ላይ ያነበብኩት ያንድ ጨካኝ የ ሮማ ንጉሥ ታሪክ ትዝ ይለኛል -  (ካሊጉላ ነው መሰለኝ)። የሮማን ሕዝብ ያለርህራሄ ሲጨፈጭፍ ኖሮ፣ አላልቅለት ቢሉ ጊዜ "ምነው ባንዴ ቆርጬ ለመጣል እንዲያመቸኝ የሮማውያን ሁሉ አንገት አንድ በሆነ!" ብሎ እንደተመኘ ተፅፏል። የሚጠላው ነገር ባንድ ፓኬጅ እንዲመጣለትና ባንዴ አጥፍቶ ለመገላገል ሲመኝ ነው ማለት ነው።  አንዳንዴ ሳስበው መለስ ዜናዊም ትንሽ ለየት ባለ መንገድ ይህንኑ የሚመኝ ይመስለኛል - "ካመት ዓመት እዛም እዚህም ከመርገጥ ምነው ይሄ 'ኢትዮጵያዊነት' የሚሉት መርዝ ከነምልክቶቹም፣ ከነ ዕምነቱም፣ ከነፍልስፍናውም አንድ ነገር ሆኖ በመጣልኝና እሱን ድፍጥጥ ባደረግኩት!

ይሄ ሳይበቃ፣  የሚያጠገው ያጣው ብሔራዊ ቁስላችን ደሞ  እያንዳንዱ የዚህ ዓይነት የጋራ ኢትዮጵያዊነት ስሜት ተጋሪ በሠላሙ፣ በነፃነቱ፣ ስንቱም በሕይወቱም ጭምር በዚህ ዕምነቱ ምክኒያት የመለስን ቂም በቀል መራራ ገፈት እንደቀመሰ ለማየት ሁላችንም የምናውቃቸውን እነ

አሥራትን፣ እነ ገብሩን፣ እነ ስዬን፣ እነ ብርሃኑን፣ እነ ኃይሉ አርአያን፣ እነ አብርሃ በላይን፣ እነ አብርሃ ያየህን እና ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ሌሎች የጋራ ብሔራዊነት፣ የመቻቻል፣ የ ዕርቅ ና ያንድነት አርበኞች መዘርዘር ይቻላል። እነዚህ ሁሉ ሰዎች ላገር ያደረጉት ትግልና የከፈሉት መስዋዕትነት መጠን እንደ ትግል መስካቸው ዓይነት፣ እንደ ሙያቸው፣ እንደየነበሩበት የፍልሚያ ሜዳና እንደዘመኑ ቢለያይም ሁሉንም የሚያገናኛቸው አንድ ነገር ኢትዮጵያዊነታቸው ይመስለኛል።

መለስ ዜናዊ ሁሉንም አምርሮ የሚጠላቸውና ፈፅሞ ይቅርታ ሊያደርግላቸው የማይችለውም በዛው ምክኒያት ብቻ ነው። ትላንት እነ አሥራት፣ ከዛ እነ ገብሩ፣ ከዛ እነ ስዬና አረጋሽ፣ ከዛ እነ ብርሃኑና ሃይሉ አርአያ፣ ከዛ፣ ስማቸውንና ተግባራቸውን ዘርዝረን የማንጨርሰው ሌሎች ሺህ በሺህ ኢትዮጵያውያን። ብዙዎቹን ሕዝብ አያውቃቸውም፣ አንዳንዶቹ ደሞ ባንድ ወይ በሌላ ምክኒያት ዝነኞች ናቸው - ሕዝብም ያውቃቸዋል።

ዘንድሮ ደሞ  ላንዴ እንደገና የመለስ ማለቂያና ምህረት የሌለው የቂም በትር አዲስ ተረኛ አገኘ!

መለስ ዜናዊ ‘ምነው የኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት፣ ያገር አንድነት፣ የህዝቦች መቻቻል፣ የዕርቅና ያብሮነት ዕምነት ባንድ አካል ተመስሎ ባገኘሁትና ላንዴም ለመጨረሻም ጊዜ ጭፍልቅ አድርጌው በተገላገልኩ’ ብሎ የቂም-በቀል ህልሙን ፍቺ ሲመኝ ቴዎድሮስ ካሣሁን የሚባል አንድ ትንሽ ልጅ ፊቱ ተፈጠረለት።

“ተዋዶ መትጋት ግን ቅጣት ያስተርያል…”፣ “እስቲ ተዋደዱ፣ በልዩነታችሁ…” ፣ “ሞፈሩን ያዙና፣ ይቅር ተባባሉ…”፣ “ጅማ ያብሮነት ከተማ…”፣ “ይጥባ ዘመኑ፣ ሁሉ ሰው ታርቆ…” ፣ “ዘመኑን ጀመርንው፣ ይኸው ታርቀን…”፣ “ይቺ ባንዲራ፣ ናት ዕድለኛ፣ ዛሬም አኮራት፣ ቀነኒ ኬኛ…”፣ “ተዋዶ ያለበት እስላም ክርስቲያኑ፣ ተዘነጋሽ እንዴ ኢትዮጵያ መሆኑ…?”

እያለ የሚያቀነቅን… እና በዚሁም ምክኒያት ኢትዮጵያዊ ሁሉ ባድናቆት የሚጦዝለት፣ ኢትዮጵያዊውን ሁሉም ባገር ፍቅር፣ በጋራ ብሔራዊነት፣ በዕርቅ፣ ባብሮነት እና በእኩል አንድነት ስሜት የሚያጦዝ አንድ ሰው ካለ… የመለስ ዜናዊ  ፀረ-ኢትዮጵያዊነት፣ ፀረ-ብሔራዊ አንድነት፣ ፀረ-አብሮነት፣ ፀረ-ዕርቅ እና ፀረ-አገራዊነት ደመኛ ሠይፍ አንገቱ ላይ ይምዘገዘግለት ዘንድ የግድ ነው!

ይኸው ነው ቴዎድሮስ ካሣሁን ላይ የደረሰው።

ለኛ እንዳለመታደል፣ ለመለስ ዜናዊ ደሞ እንደ ዕድል ሆኖ የሮማው ካሊጉላ የሮማዊያን ሁሉ አንገት አንድ በሆነልኝና ባንዴ ቀንጥሼ በጣልኩት ብሎ የተመኘው ሳይሆንለት፣ ንጉሥ መለስ  “ይኼ ‘ኢትዮጵያዊነት’ የሚሉት ቅዠት ምነው አንድ አካል ሆኖ በመጣልኝና ባንዴ ድፍጥጥ አድርጌው በተገላገልኩ” ብሎ ሲመኝ ቴዎድሮስን አገኘ!

ለመለስ ዜናዊ፣  ኢትዮጵያዊነት ላይ ያቄመውን ያርባ ዓመት በቀል ለመወጣት ከቴዎድሮስ የተሻለ የተሟላ ፓኬጅ ያለ አይመስለውም - ምናልባት ዕውነቱንም ነው። ምንም ልጅ ቢሆን የቴዎድሮስ ስብዕና ከዕድሜው በላይ ገኗል። ይህ ስብዕናውም በማያከራክር ዓይነት የተመሠረተው በዛው መለስ ዜናዊን እጅግ በሚያንገሸግሸው የ ‘ኢትዮጵያዊነት’  ብሔራዊ ስሜት ላይ ነው። ዕድሜው ምናልባት ከመለስ ዜናዊ ከ 30 ዓመት በላይ ቢያንስም በዚህ ዘመን ባንድ ወይ በሌላ መንገድ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ጉዳይ ላይ እያሳደረ ያለው ተፅዕኖ (in its own way) ከመለስ ጋር ሊስተካከል ሁሉ ይደርሳል (ይሄን ለመረዳት ሁላችንም ከምናውቀው ያገጠጠ ሃቅ በተጨማሪ አዲስ ፎርቹን የሚባል

ኢትዮጵያ የሚታተም የእንግሊዝኛ ጋዜጣ በኢትዮጵያ ሚሊኒየም ማግሥት ሁለቱን - ቴዎድሮስንና መለስን - እያወዳደረ የፃፈውን ድንቅ ርዕሰ-አንቀፅ ማንበብ ሳይረዳ አይቀርም)።

ስለዚህ፣ ቴዎድሮስን ማሰር፣ ማንገላታት፣ ማማረር፣ ተስፋ ማስቆረጥ፣ ማሰቃየት፣ ማረኝ እንዲል ማስገደድ፣ ማስፈራራት፣ ማስራብ፣ ማቆሸሽ፣ በሽታ ላይ መጣል እና ስሜቱን መግደል ለመለስ ዜናዊ ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ መምታት፣ ወይም እንደ ካሊጉላ ምኞት የ 'ኢትዮጵያዊነት'ን ዕምነት አንድ ቦታ ላይ ተቆልሎ ማግኘትና ያለርህራሄ መቀጥቀጥ መቻል ነው።

ልጁ - በዘፈኖቹ፣ በቃለ-ምልልሶቹና በንግግሮቹ በሚያጕላው ብሔራዊ ስሜት ምክኒያት እንደ ግለ-ሰብ ለመበቀል ከመንገብገብ ባሻገር፤ በፖለቲካ ሳይሆን በኪነ-ጥበብና አርት ኢትዮጱያዊነትን፣ አብሮ መኖርን፣ መቻቻልን፣ ይቅርታን፣ የጋራ ብሔራዊ አንድነትንና እኩልነትን መለስ ባላሰበው መንገድ እያደነደነ ስለመጣ መቀንጠስ አለበት! ይህ ሲሆን፣ ልጁ እንደ ግለ-ሰብ ስለ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊነት እየተፈላሰፈ 'መባለጉ' ሳያንስ ቀስ በቀስ ሕዝቡን ሁሉ ማሰለፍ እየጀመረ ስለመጣ እሱን በፈጠራ ክስ ማግለል ይህንን 'አደጋ' ያስወግዳል። ሁለተኛ ደሞ መለስ ጨርሶ ባልተዘጋጀበት በቴዎድሮስ ምክኒያት በተፈጠረው የአርት፣ የኪነጥበብና popular culture ፍልሚያ ሜዳ ይሄ 'ኢትዮጱያዊነት' አልሞት እያለ ስላስቸገረ፣ የ 'ኢትዮጵያዊነት' እና ያብሮነት ተዋጊዎች የፍልሚያውን ዘዴ በቴዲ ዓይነት ሠላማዊ የፍቅርና ያንድነት ዘመቻ ከቀየሩ ካዝማቾቹ አንዱንና ምናልባትም ዋነኛውን ተዋናይ 'ሰው ገጭቶ ገሏል' ብሎ ከማሰርና ከማስወገድ ሌላ የተሻለ መፍትሄ የለም! ሁላችንም ልንረዳው እንደሚገባን ቴዎድሮስ የታሰረው በዛ እና በዛ ምክኒያት ብቻ ነው። የመታሰሩ ዋና ምክኒያት አንድ ሰው ተገጨ፣ አንድ ሰው ሞተ፣ አንድ ሰው መንጃ ፈቃድ አልነበረውም፣ አንድ ሰው ምስክር ነው፣ አንድ ሰው ገጭቶ ጠፋ፣ አንድ ሰው አይቶታል። ተገጪው ድሃ ነው፣ ገጪው ሃብታም ነው … አይደለም!

በግልፅ እንደሚታየው የቴዎድሮስ ወንጀል ይሄ አይደለም። ወንጀሉ 40 ዓመት ሙሉ ይሄን አስተሳሰብ ለማውደም ሌት ተቀን ያለ እንቅልፍ የታከተው መለስ እንኳን ሊቋቋመው ያልቻለው የኢትዮጵያዊነት፣ የአንድነትና ያብሮነት አስተሳሰቡ ነው!

በመሆኑም የቴዲ መታሰር ያገር መታሰር ነው፣ የኢትዮጵያዊነት መታሰር ነው፣ ያንድነትና ያብሮ መኖር መታሰር ነው። የይቅር ባይነትና የደግነት መታሰር ነው፣ የሰብዓዊነት ህልምና የኢትዮጵያዊነት ተስፋ መታሰር ነው።

ስለዚህም ነው ቴዎድሮስ ካሣሁንን በምንም ምክኒያት ማሰር ቴዲን እንደግለሰብ ከማሰቃየት በላይ በሠላማዊ መንገድ፣ በ አርት፣ በሥነ-ጥበብና በኪነት ኢትዮጵያዊነትን ከሞት ለማዳን የሚደረገውን ትንቅንቅ ለማኮላሸት የታለመ እጅግ የተረገመ መሠሪ ሴራ የሚሆነው። አለመታደል ሆኖ ለመለስ ድሉ ባለ ሁለት አንጓ ነው። ቴዎድሮስ የሚባል አስጊ ብላቴና በመታሰር ወይ ተስፋ በመቁረጥ ከመንገዱ ይወገዳል፤ ሌሎች የሱ ቢጤዎች ደሞ እሱ የደረሰበትን (እና መለስ ሊያደርግ የሚችለውን) ዓይተው መንቀዥቀዣቸውን ያቆማሉ። በሁለቱም መንገድ 'ኢትዮጵያዊነት' የሚሉት ቅዠት ተጨማሪ ሁለት ርምጃ ወደማይቀረው ሞቱ ይራመዳል። መለስ ከነመርዝ ሰንኮፉ እንደገና 'ሊያሸንፍ' እኛም ከነቅንነታችን እንደገና ሌላ ሞት ልንሞት ነው!

አይበቃም?

"ኤሎሄ ... ኤሎሄ… ላማ ሰበቅታኒ!"

(dawit_aberru@yahoo.com.au)